# ፓኖራማ ቁጥር 83

## የትዝብት አድማስ

ታህሳሥ 14 ቀ ን 2002 ዓም

### እናቱን ከሸጠ ምን ደግ ይጠበቃል?

በዚህ ባለፈው ሳምንት መጀመሪያ የአየር ንብረት ዓለም አቀፍ ጉባዔ በዴንማርክ ዋና ከተማ ኮፐንሀገን ላይ ተካሂዷል ። የወያኔው መለስ ዜናዊም የአፍሪካ አህጉር አፈ-ቀላጤ ነኝ ብሎ በስብሰባ መገኘቱ ተገልጿል ። ወደ ጉባዔው የሄዱት ክፍሎች ሁለት ነበሩ ። የመጀመሪያዎቹ በኢንዱስትሪ የገፉና የበለፀጉ ሀገሮች በመሆናቸው የኢንዱስትሪውን ማኅበረሰብ የሚወክሉ ነበሩ ። ሌሎቹ ደግሞ በኢንዱስትሪ ወደኋላ የቀሩና ደሀ አገሮች የሚባሉትን የሚወክሉ ነበሩ ። ሁለቱም ወደ ጉባዔው ያመሩት የየራሳቸውን ጥቅም እናስጠብቃለን በማለት ነበር ። በኢንዱስትሪዎች መብዛትና በሌሎችም ሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት የአየር ንብረቱንና የተፈጥሮ አካባቢዎቹን የመረዘው ብክለት ያስጨነቃቸው የበለፀጉ ሀገሮች ወደዚህ ጉባዔ የሄዱት ፥ የራሳቸውን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ነው ። የአፍሪካ ሀገሮችም እንደዚሁ ወደዚህ ጉባዔ ያመሩት ሰሚ ካገኘን፥አህጉራችንን ከአየር ብክለት አደጋ ለመከላከል የሚያስችለንን ውሳኔ እናገኛለን የሚል ተስፋ ቋጥረው ነበር ። የአፍሪካውያን ተስፋ ግን በምዕራባውያን ትዕዛዝና ተፅዕኖ ሰበብ መለስ ዜናዊ በፈፀመው አሳፋሪ ክህደት ዕውን ሊሆን አልቻለም ። ይህ የመለስ ክህደትና ለምዕራባውያንም ያለው አጎብዳጅነት፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ ስለአልሆነ እኛን ሊያስገርመን አልቻለም ። ወልዳ ያሳደገችውን ኢትዮጵያን የሸጠና ሕዝቧንም የከዳ ግለሰብ ለሌላው ሀገር ጥቅም ይቆማል ብሎ ማሰብ ፥ መጀመሪያውንም የመለስን ባኅርይና ድርጊት አለመገንዘብ ነው:: አፍሪካውያን ሀገሮች በዚህ ጉባዔ እድትወክላቸው የመረጧት ኢትዮጵያን እንጅ ክህዲውን መለስን አልነበረም ። መለስን የሚያሽሞነምኑትና የሚንከባከቡት ምዕራባውያን ካልሆኑ በስተቀር የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳልሆነ በአሁኑ ወቅት መላው ዓለም ተገንዝቦታል:: በኢትዮጵታ ላይ ዘረኛ ሥርዓትን መስርቶ ሕዝቧን የከዳ ግለሰብ፥የአፍሪካን አህጉር ሊወክል አለመቻሉን በክህደት መግለፁ ፥ የአፍሪካ ሕዝብ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ያለውን ክብርና ዕምነት ከቶ አይቀንሰውም ። የኢትዮጵያና የአፍሪካ አኅጉር ሕዝቦች

ዝምድናም ሆነ ግንኙነት ታሪካዊ እንጅ በዲፕሎማቲክ አግቦ ብቻ የሚወሰን አይደለም ። በታሪክ ብቸኛው ነፃ አፍሪካዊት ሀገር የነበረችው ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ቀንበር የነበሩትን የአፍሪካ ሕዝቦች ከቅኝ ግዛት ባርነት ተላቅቀው ነፃነታቸውን እንዲጎናፀፉ ግንባር ቀደም ሚና መጫወቷ፥ ለአባባላችን መሠረት ይሆነናል ። መላው የአፍሪካ አኅጉር ከቅኝ ግዛት ቀንበር ከተላቀቀም በኋላ ፥በአፍሪካ ሀገሮች መካከል ለተፈጠሩት ልዩልዩ ችግሮች መፍትሄ ለማምጣት የበኩሏን አስተዋፅዖ ስታደርግ ቆይታለች ። የመለስ ዜናዊ ለምዕራባውያን አጎብድዶ የአፍሪካን ጥቅም መካድ ይህንን ሀቅ ታሪካዊ አይለውጠውም ።

በዚህ በዴንማርኩ ያየር ጠባይና የካባቢ እንክብካቤ ጥበቃ ዓለም አቀፍ ጉባዔ ላይ፥ መለስ ዜናዊ ከፈረንሳዩ ፕሬዝዳንት ከኒኮላስ ሳርኮዚ ጋር በመመሳጠር አፍሪካን የሚጎዳ ውሳኔ ለማሳለፍ ተስማምቷል። ኃሳቡን ፥ የአየሩን ሙቀት ሁለት ዲግሪ ሴንትግሬድ ከቅድመ-ኢንዱስትሪ ልኬታ በላይ ያደረርገዋል ተብሎ ስለተፈራ መላው የአፍሪካ መልዕክተኞች ተቀውመውታል ። የመላው አፍሪካ አየር ጠባይ ተንከባካቢ ድርጅት
( CLIMATE JUSTICE ALLIANCE )
ይህንን ኃሳብ በማውገዝ ተቀውሞታል ። ከዚህም በቀር ሌሎች የአፍሪካን አየር ብክለት የሚቆጣጠሩ ተቋማት ሁሉ ስምምነቱ፥የአፍሪካን የልማት እንቅስቃሴ በብርቱ እንደሚጎዳው ያላቸውን ስጋት በመግለፅ የመለስን ክኅደት ኮንነዋል ። እንደ አየር ጠባይ ሊቃውንት አመለካከት ከሆነ፥ ሁለት ዲግሪ ሴንቲግሬድ ማለት የአፍሪካን አኅጉር ልኬታ ወደ ሦስት ነጥብ አምስት ዲግሪ ሴንትግሬድ ከፍ ያደርገዋል ተብሏል ። በዚህ ጉባዔ የተሳተፉት፥የናሚብያ ጠቅላይ ምኒስትር ንሃስ አንጎላ፥ የዩጋንዳው የውሃ ሀብት ምኒስትር ፥ ወይዘሮ ማርያ ሙታጋምባ ፥ የሌሴቶ መልዕክተኞች መሪ ምስተር ብሩኖ ሲኮሊ ይህ በመለስና በፈረንሳዩ ፕሬዝደንት የቀረበው ኃሳብ በሚሊዮን የሚቆጠሩትን የአፍሪካን ሕዝቦች ህይወት ፥ ኢትዮጵያንም ጨምሮ እንደሚጎዳ አስጠንቅቀዋል ። ከሁሉም በበለጠ የመለስ ዜናዊን ክህደት ነጥብ በነጥብ የተቃወሙት ፥በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ ጂ-77 ተብለው የሚጠሩትን ሀገሮች በመወከል በጉባዔው ላይ የተገኙት ሱዳናዊው ዲፕሎማትና የጉባዔው ተደራዳሪ፥ሚስተር ሊሙባ ዲያፒንግ ናቸው ። በዲፕሎማሲው ማኅበረሰብ ዘንድ የተራቀቀ ችሎታ አላቸው ተብሎ የተመሰከረላቸው እኝህ ሱዳናዊ የዓለም አቀፍ ድርጅት ተወካይ መለስና የፈረንሳዩ ፕሬዝዳንት ኔኮላስ ሳርኮዚ ያቀረቡት ኃሳብ ያፍሪካን ሕዝብ በእሳት ዲን ሊያቃጥላት የሚችል ፍርድ ነው ብለውታል ። ይህ ስምምነት በሥራ ላይ የሚውል ከሆነ፥አውሮጳውያን ስድስት ሚሊዮን ሕዝብ ወደ ሆሎኮስት/ ፍጅት አስገብተው እንደ አስጨረሱት የሚቆጥር የአረመኔ ባኅል እንደሆነ አስረድተዋል ። መለስ ዜናዊ ያፍሪካን ሕዝብ የሸጠበትን ይህንን የክህደት ድርጊት በሦስት ምክንያቶች ዋጋ እደማይኖረው በመግለጫቸው አብራርተዋል ።

ይኸውም

አንደኛ፡- የሳይንስ ምርምርን በብዛት ያላካተተና የአፍሪካንም ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ በመሆኑ÷የአፍሪካን ሕዝቦች የልማት አቃጣጫ የሚያስት ነው ። የነዋሪዎቹንም ሕይወት ይጎዳል ።

ሁለተኛ ፡- ነፃ ግምገማ ያልተደረገበት ከመሆኑም በቀር የሌሎቹን ባለሙያዎች ምክርን ጠይቆ በግምት ውስጥ ያላስገባ ነገር ግን በኢንዱስትሪ የገፉትን ሀገሮች ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅ ሲባል የተዘጋጀ ነው ። ነፃዋ አፍሪካ በምዕራባውያን ተፅዕኖ በቀረበ ረቂቅ ውሳኔ የሞት ፍርድ ሊፈረድባት አይገባም። የዚህ ክህደት ተባባሪዎች ሁሉ ተጠያቂዎች ይሆናሉ።

ሦስተኛ ፡- በጥድፊያ የተዘጋጀ በመሆኑ ሁለንተናዊ እይታ የጎደለው ነው ። ሲሉ አብራርተዋል።

በዚህ በኮፐንሀገን ጎባዔ የተገኙት የናሚብያው ጠቅላይ ሚኒስቴር ነሀስ አንጎላና የሎሴቶው መልዕክተኞች መሪ ቡሩኖ ሲኮሊ የፈረንሳዩን ፐሬዝዳንት ተፅዕኖና የመለስን ክህደት አውግዘዋታል። እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ከ 2020 ዓመተ ምህረት በኋላ ሊገኝ ይቻላል የተባለው የ100 ቢሊዮን ዶላር ርዳታ÷ ልክ በሠላሳ ብር የአፍሪካን ሕዝብ እንደ መሸጥ የሚቆጠር ታላቅ ክህደት ነው ተብሏል ።

የምዕራባውያን አገልጋይ የሆነው መለስ ዜናዊ÷እንኳንስ የመላው አፍሪካን ሕዝቦች ጥቅም ይቅርና ኢትዮጵያንም የማይወክል መሆኑን እርሱ ባለቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወስኖ ያለበት ሁኔታ ነው ። በመሆኑም ይህ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ሂጄ ያፍሪካ አህጉር አፈ-ቀላጤ ሆኛለሁ ብሎ በዚህ በኮፔን ሀገን ጉባዔ በመገኘት ክህደት የፈፀመው መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ከቶ ሊወክል አይችልም ። የፈፀመውንም የክኅደት ድርጊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውግዘዋል ። ለአለፉት አስራ ዘጠኝ ዓመታትም በኢትዮጵያ ስም የፈፀመውን ብሔራዊና አህጉራዊ ክኅደትና ወንጀል ኢትዮጵያና ዜጎቿ ይኮንኑታል ። ይቃወሙታል ። መለስ ዜናዊና ምዕራባውያን የሚጠነስሷቸውን ሀገራችንን የሚጎዱ ማንኛቸውም ስምምነቶች ÷ ድርድሮችና ውሳኔዎች ሁሉ ህጋዊነት አይኖራቸውም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን አስወግዶ በሚያቋቁመው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት÷ በነመለስ ዜናዊ ምክንያት ሀገሩ የተነጠቀችውን ብሔራዊ ጠቅሟን ሁሉ የማስመለስ ሕጋዊ መብቷን የምትጠቀም

መሆኗን አሁንም በማስረዳት ላይ ትገኛለች ። መለስ ዜናዊ በዚህ በኮፔን ሀገን የአየር ጠባይ ጉባዔ ላይ የፈፀመው ክህደት የጎዳው መላውን ያፍሪካን ሕዝብ መሆኑ ባይዘነጋም፥ ምዕራባውያን የጡት አባቶቹን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲል በተለያዩ ሁኔታዎች የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም ሲያስደፍርና ሲጎዳ እንደ ነበረ ዛሬ ያፍሪካ ሕዝብ ለመረዳት መልካም አጋጣሚ ሆኖለታል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት ምን ያህል ብሔራዊ ችግር እንደገጠመውም ተገንዝቦለት፥ መላው የአፍሪካ አኅጉር ሕዝብ ፥ ሀገሩ ኢትዮጵያ ከዘረኛ አምባገነን አገዛዝ ነፃ ለማውጣት በሚያደርገው ትግል ትብብሩን እንደሚያደርግለት ይጠበቃል ። ይህ ካልሆነ ግን፤ ብቸኛዋና ነፃዋ ሀገራችን፥ በኢጣሊያን ፋሽስት ወረራ ጦስ መላው ዓለም በጦርነት ማዕበል እንደተጠቅለቀለቀ ሁሉ ፥ የኢትዮጵያ መጥፎ ዕድል በኢትዮጵያ ወሰን ብቻ ተገድቦ እንደማይቀር አስተዋይ ኅሊና ያለው ሁሉ ይገነዘበዋል ብለን እናስበልን ።ኢትዮጵያ እየተቃጠለች ወላፈኑ ወደሌሎች አይዛመትም ለማለት ያስቸግራል። በታሪክ፥ ኢትዮጵያን እናጠፋለን ብለው የተነሱት ሁሉ፥እነርሱ ጠፉ እንጅ፥ሀገራችን ግን ዘለዓለማዊት ሀገር ሆና ቀጥላለች። ወደፊትም ትቀጥላለች ። የኢትዮጵያን ማንነት እያጠፋ ያለ ከሀዲ ቡድን ፥ የአፍሪካን ጥቅም ለያስጠብቅ ይችላል ብሎ መጠበቅ ከታሪክ አለመማር ነው ። በመሆኑም፥ መለስ ዜናዊና ቡድኑ ሀገርን የሸጡ ፤ የካዱ ናቸውና አፍሪካንም ቢክዱ የሚገርም አይሆንም።

እየታገሉ መሰዋት፥ እየተሰው ሀገር ማዳን ታሪካችን ነውና ትግላችንን እንቀጥላለን !!!!